ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር

**KINIJIT NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS (KNAASO)**

766 Rock Creek Church Rd. NW. Washington DC. 20010

Tel: (202) 541 0556 Fax: (202) 541-0557 Email: kinijitna@kinijitna.org


ጃንዋሪ 28 2008 ዓ/ም

# የሕዝብን ልጆች በማፈን የዴሞክራሲ ትግል አይገታም!

ኢሕአዴግ የውጭ መንግሥታትን ልብ ለማነሁለልና ዳረጎት ለማግበስበስ አለፍ አለፍ እያለ በዲሞክራሲ ስም ቢምልም ውስጠ ባሕርይው አሁንም ጸረ ዲሞክራሲ መሆኑን የሚያረጋግጡ የወከባና የእስራት ነውሮችን ከመፈጸም አልተቆጠበም።

በዛሬው ዕለት የመንግሥት ወታደሮች አቶ አለማየሁ አንተነህ የተባሉትን የቅንጅት የደቡብ ክፍል አስተባባሪና አቶ ግርማ አማረ የተባሉትን የቅንጅት የሕግ ቡድን አባል ያለአንዳች ምክንያት ከቢሮ ወስደው እንዳሠሯቸውና አንገላተው እንደለቀቋቸው ሰምተናል። እነዚህ ሁለት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ለዴሞክራሲ፤ ለሰብአዊ መብትና ለሀገር አንድነት በመቆማቸው ብቻ ከሌሎች የቅንጅት አመራሮች ጋር በቃሊቲ የማቀቁ፤ ከእስር ከወጡ በኋላም እንደወትሮው ሁሉ የሠላማዊ ትግልን መርህ ተከትለውና ሕገመንግሥቱ የሚፈቅድላቸውን መብት ተጠቅመው የሚንቀሳቀሱ ዜጎች ናቸው።

የኢሕአዴግ መንግሥት የብዙ ሚሊዮን ሕዝብ ራዕይ መገለጫ የሆነውን የቅንጅትን እንቅስቃሴ ለማዳከም፤ ከቻለም ለማጥፋት ግልጽና ስውር ጥቃት እየፈጸመ መሆኑን መላው ሕዝባችንና መላው ዓለም ያውቁታል። በአንጻሩ ደግሞ ቅንጅት በጠርነትና በአምባገነኖች መዳፍ ስር ለዘመናት የተጎሳቀለች ሃገራችን ዳግም በዚያ መስመር እንዳትጎተት የሠላማዊ ትግል አርማ አንስቶ አዲስ ተስፋ ያሰጨበጠ የሃያ አንደኛው ክፍለ-ዘመን ፓርቲ ነው። ይህ የሠላማዊ ትግል ሰንደቅ ኢሕአዴግን ከጦር የበለጠ የሚረብሸው ስለሆነ ቅንጅትን ያልሆነ ስም ለመስጠትና አባላቱም እንዲማረሩ ለማድረግ ሲያዋክብ፤ ሲያስርና ሲፈታ እናያለን። የቅንጅት መሪዎችና አባላት ሠላማዊ ትግል እልህ አስጨራሽና መስዋዕትነት ጠያቂ እንደሆነ አውቀው ወደትግሉ መስክ የተሰማሩ ስለሆኑ ይህን ቁርጠኝነታቸውን የሚያስለውጥ ምንም ዓይነት ወከባና እስራት ሊኖር አይችልም።

በውጭ የምንኖር ዜጎች የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ትግላችንን ከምንጊዜውም በበለጠ አቀናጅተን የምንንቀሳቀስበትን መንገድ የቀየስን ስለሆነ የሀገር፤ የወገን፤ የዴሞክራሲና የቅንጅት አለኝታነታችን ጎልቶ ይቀጥላል። የ97 ምርጫ፤ ዓለም አቀፍ የዲሞክራሲ እንቅስቃሴና በቅርቡም በጎረቤት አገር የተከሰተው ተመክሮ ለኢሕአዴግ ትምህርት ሰጭ ስለሆነ ብሔራዊ ስምምነት የሚመጣበትን መንገድ እንዲያመቻች አሁንም ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። ቅንጅት በማይገታ የዲሞክራሲና የሠላም ባቡር ውስጥ የሚጓዝ ፓርቲ ነውና ይህንን ዕውንታ ተገንዝቦ ከመሰሪና አምባገናንዊ ድርጊቶቹ እንዲታቀብ እናስገነዝባለን።

**ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር**

**ሠላማዊ ትግል ብቸኛው የቅንጅት ጎዳና ነው!**
**የመብትና የዴሞክራሲ ጉዞ በወከባ አይገታም!**